# የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ)

*Ethiopian People´s Revolutionary Party (EPRP)*

ነሐሴ 7/2010

## <u>በግፍ የዜጎችን ሕይወት ማጥፋቱ በአስቸኳይ ይቁም</u>

በኢትዮጵያ አሰቃቂና በጣም አሳሳቢ የሆኑ ሁኔታዎች እየተመለዱ መምጣታቸው በጉልህ የሚታይ ክስተት ሆኗል። ሕዝብን እርስ በርስ የሚያፋጁ አውሬዎች ነጻ ተለቀው ዜጎችን ለከፋ እልቂትና አደጋ አጋልጠዋል ። ጅግጅጋ፤ድሬ ዳዋ ሶማሌዎች፤ኦሮሞዎች አማራዎች፤ጉራጌዎች ወዘተ መፈናቀል ብቻ ሳይሆን በአሰቃቂ ሁኔታ ተገድለዋል ። ጌዴዎ-ኦሮሞ፤ቤኒሻንጉል አማራ፤ሻሸሜኔ፤ቦረና ገሬ፤ትግሬ ወሎ ሕዝብ በየምክንያቱ እየተፈጀ፤ ንብረቱ እየወደመበት ለዓመታት ከኖረበት ቤትና ቀዬ እየተፈናቀለ ይገኛል። ኢሕአፓ ይህን ክስተት በጥብቅ እያወገዘ ሕዝባችን  በወያኔ  የተንኮል ድር ተጠልፎና ተከፋፍሎ ወደ እልቂት እንዳያመራና ሀገራችን ኢትዮጵያን ለጥፋት እንዳይዳርግ በጥብቅ ያሳስባል ።

እየተከሰተ ያለው ሁኔታ ለአገራችንንና ለሕዝባችን አደጋን ያዘለና ይህ ነው የማይባል ጥፋትን ያረገዘና መውለድም የጀመረ ነው ። ወያኔ ሥልጣኑን ጠግኖ ለመቀጠል በየቦታው ያጠመደውን የክፍፍል ፈንጂ ማፈንዳት ጀምሯል ። የኢትዮጵያ ሰላምና መረጋጋት አደጋ  ላይ ወድቋል በሚል ላቀደው  የመፈንቅል መንግሥት እርምጃ ማጠየቂያ እያዘጋጀ ነው ። ፍቅር ሰባኪዎቹ አዳዲስ ሹሞች ይህ የሀገር አንድነት እንዴት በዴሞክራሲ ሊጠበቅ እንደሚችል ከሰብካው ባሻገር ያወቁበት አይመስልም።  በጸረ ኢትዮጵያ አንድነት የታወቁና የማሉ ጠላቶችን በዙርያቸው በመሰብሰብና የአንድነት ስይሆን የክፍፍልና የጥበት እርምጃዎችና አቅዋሞችንም እየወሰዱ መሆናቸው ዓይኑን ለከፈተ ዜጋ ሁሉ አሳሳቢ ሆኖ የሚከሰት ሆኗል ። በጥበትና በጥላቻ ነውረኛና ጸረ ሕዝብ ድርጊቶችን-- ወንጀሎችን-- የሚያበረታቱ  ወንጀለኛ ኃይሎች ሁሉ የክብር እንግዳ ሆነዋል ። አገዛዙ የሽግግርን ሂደት ሰርዞ የግለሰብና የቡድን አምባገነንነት እንዲቀጥል  መምረጡ ራሱ ላለው አስከፊ ሁኔታ መንገድ ጠራጊ መሆኑ ክርክር አያሻውም ።

ኢሕአፓ ለተገደሉትና ለተጨፈጨፉት ዜጎች ቤተሰቦች ሁሉ ጽናትን ይስጣችሁ ይላል ። ይህ የግፍና የፍጅት ሁኔታ ተከስቶ እንዳይቀጥል የወያኔን አገዛዝ አስወግደን ዴሞክራሲያዊ መንግሥት እንመስርት ሲልም ታግሷል ፤ አሁንም እየተጋለ ነው ። የወያኔ ኢሕአዴግ ስርዓት ተጠግኖ ቢሆንም እስከቀጠለ ድረስ በጅጅጋ ድሬ ዳዋ ወዘተ የተከሰተው ሀገር አሳፋሪ ዕልቂትና ግድያ መቀጠሉ ከቶም የሚቀር አይደለም ። ይህን በመገንዘብ የሀገራችንን ህልውናና የሕዝባችን ደህንነት ለመጠበቅ ጸረ ወያኔ ጸረ ኢሕአዴግ ትግላችን እንዲቀጥል ጥሪያችንን እንደግማለን ። በወያኔ ዋና አነሳሽነት በሕዝብ መሃል የተቀሰቀሰው ግጭትና ግድያ በአስቸኳይ ሕዝብ እንዲያቆመውም ጥሪያችንን እናስተላልፋለን ።

የኢትዮጵያ ህልውና በደማችን ይጠበቃል!!

ጸረ ወያኔው ትግል ተፋፍሞ ይቀጥል !!

የኢትዮጵያ ሕዝብ አንድነት ይጠናከር !

**EPRP**
**P.O.BOX  73337**
**Washington DC,  20056**
**USA**

**Email  ESPIC@aol.com**
**Website  WWW.EPRP.com**

**EPRP**
**BP  30022**
**92276 Bois Colombes cedex**
**France**

**Tel.  202 291 4217    Fax:  202 291 7645**